DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

ሰኔ (June) 2011

# ልጅዎ ለ 2011-2012 የትምህርት ዓመት ዝግጁ እንዲሆን ያድርጉ

የ 2010-2011 የትምህርት ዓመት እየተገባደደ በመምጣት ላይ ባለበት ወቅት፣ የቀጣዩ ዓመት የትምህርት መጀመሪያ ቀን በሆነው **ሰኞ፣ ነሀሴ (Aug) 22, 2011** – ላይ እይታችንን ስናሳርፍ ሁላችንም እስከ ዛሬ ባጠናቀቅናቸው ክንውኖች ላይ ጠለቅ አድርገን ማሰብ እንችላለን። ከዚህ በታች ለ 2011-2012 ስኬታማ የትምህርት ዓመት ጅማሬ ለመዘጋጀት የሚረዱዎ ጥቂት ማሳሰቢያዎች ቀርበልዎታል። ለተጨማሪ መረጃዎች እና አዳዲስ ሁኔታዎች **የዲሲፒኤስ ድረገጽ የሆነውን፣ dcps.dc.gov ን በበጋው ወቅት በሙሉ እባክዎን ይቃኙ።**

## ለ 2011-2012 እና ለትምህርት በኋላ አገልግሎት መርሀ ግብር አሁን ይመዝገቡ

**እባክዎን በተቻለዎት መጠን የልጅዎን ዓመታዊ የመመዝገቢያ ቅጽ አሁኑኑ ለልጅዎ ትምህርት ቤት ወስደው ያስረክቡ።** ቀደም ብሎ መመዝገብ ዲሲፒኤስን ለስኬታማነት ዓመት ለማቀድ ይረዳዋል። **የመመዝገቢያ ቅጾች፣ ከልጅዎ ትምህርት ቤት ወይንም dcps.dc.gov. ድረገጽ ላይ ይገኛል።** ስለ ምዝገባው ሂደት ማናቸውም ዐይነት ጥያቄ ካለዎት፣ እባክዎን የልጅዎን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ። ወይንም ለዲሲፒኤስ ጽሕፈት ቤት **202-478-5738** ይደውሉ።

ልጅዎን፣ በተመረጡ የዲሲፒኤስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወይንም የትምህርት ምድረ ግቢዎች፣ **ከትምህርት በኋላ አገልግሎቶች ውስጥ ለማስመዝገብ፣** ነሀሴ (Aug) 15 ቀን በሚውልበት ሣምንት ውስጥ ትምህርት ቤትዎን እባክዎን ይጎብኙ። ዲሲፒኤስ በበላይነት የሚመራቸውን ከትምህርት በኋላ መርሀ ግብሮች አገልግሎቶችን የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች በዲሲፒኤስ ድረገጽ ላይ ይገኛሉ። ስለ ከትምህርት በኋላ ፕሮግራም እና እንዲሁም ስለ የጋራ ክፍያዎች የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎን የዲሲፒኤስ ድረገጽን ይቃኙ።

## ወጣት ተማሪዎች፤ ለለጋ የልጅነት የሽግግር ሣምንት ተዘጋጁ

የቅድመ ትምህርት (preschool) እና የቅድመ መዋለ (pre-K) ሕጻናት ልጆች፣ የመጀመሪያው የትምህርት ሣምንት **የለጋ የልጅነት የሽግግር ሣምንት፣ (Early Childhood Transition Week (ECTW))** በመባል ይታወቃል። በዚህ ዓመት፣ ECTW **በየቤቱ በመገኘት ጉብኝቶች ማድረግ** ይጀምራል። **ወይንም ከነሀሴ (Aug) 22-24 ባሉት ቀናት የወላጆች ስብሰባዎችን** ያካሂዳል። **በእነዚህ ቀናት ውስጥ፣ የቅድመ ትምህርት( Preschool) እና ቅድመ መዋዕለ ሕጻናት (pre-K) ልጆች ወደ ትምህርት ቤት አይመጡም።** የሚገናኙበትን ጊዜ ለመወሰን የልጅዎ መምህር ፈልጎ ያነጋግርዎታል። ከዚህ በኋላ፣ **ከ ነሀሴ (Aug) 25-26፣ ልጆች በሁለት አነሥተኛ ቡድኖች ወደ ትምህርት ቤት ይመጣሉ።** (ልጅዎ ወደ ትምህርት ቤት የሚመጣበትን ቀን ለማወቅ ከዚህ በታች የቀረበውን ይመልከቱ።) ተጨማሪ መረጃዎች በዲሲፒኤስ ድረገጽ ላይ ይገኛሉ።

- **ለቅድመ ትምህርት/ቅድመ መዋዕለ ሕጻናት (preschool/pre-K children) ልጆች ነሀሴ ( Aug) 22-24 ትምህርት አይኖራቸውም።** (እነዚህ ቀናት ለወላጅ/መምህር ስብሰባዎች የተያዙ ናቸው።)
- **የመጨረሻ ስማቸው ከ A – K ባለው ሆሄ የሚጀምር** ልጆች፣ **ሐሙስ ነሀሴ (Aug) 25** ትምህርት ይማራሉ።
- **የመጨረሻ ስማችው መነሻ ሆሄ ከ L - Z ባለው ሆሄ የሚጀምር** ልጆች ትምህርት ቤት **ዐርብ፣ ነሀሴ (Aug) 26** ይሄዳሉ።
- **ሁሉም የቅድመ ትምህርት (preschool) እና ቅድመ መዋዕለ ሕጻናት** (pre-K) **ሰኞ፣ ነሀሴ (Aug) 29** ወደ ትምህርት ቤት ይመጣሉ።
- **በሞንቶሶሪ (Montessori)** የትምህርት መርሀ ግብር **የተመዘገቡ ልጆች** የተለየ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ሊኖራቸው ይችላል። **ለበለጠ መረጃ ትምህርት ቤትዎን ያነጋግሩ።**

## የልዩ ትምህርት ተማሪዎች የመጓጓዣ ጉዳይ መረጃዎች ወቅቱን የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ አለባቸው

የልጅዎ **ግላዊ የትምህርት እቅዱ** (IEP) **በ 2011-2012 የትምህርት ዓመት መጓጓዣ ለማግኘት ብቁ የሚያደርገው/ርጋት ሆኖ ከተገኘ** አስፈላጊ እና ተገቢ መጓጓዥ ነክ መረጃ የቀረበ ለመሆኑ በልጅዎ ትምህርት ቤት **የልዩ ትምህርት አስተባባሪውን ወይንም ርእሠ መምህሩን** በማነጋገር እባክዎን ያረጋግጡ። አንዳንድ መረጃዎች የተለወጡ ሊሆን ስለሚችል፣ እባክዎን የትምህርት ቤትዎ የልዩ ትምህርት አስተባባሪው፣ ስለ ልጅዎ መሳፈሪያ ቦታ እና ከትምህርት በኋላም ተመልሶ ስለሚወርድበት ቦታ ትክክለኛ አድራሻ እንዲሁም ስለ ትምህርት ቤቱ መገኛ አድራሻ እጅግ ወቅቱን የጠበቀ መረጃ ያለው ስለመሆኑ እርግጠኛ ይሁኑ። **የልዩ ትምህርት አስተባባሪውን ወይንም ርእሠ መምህሩን ለማገኘት ችግር ከገጠመዎ፣ በ 202-442-5400 ስልክ ይደውሉ።**

## የተለዩ ሁኔታዎች ተመቻችተው እንዲገኙለት (Accommodations) የሚያስፈልገው ተማሪ ያውቃሉ?

**ዲሲፒኤስ በፌደራላዊ ሕግ መሠረት** (known as Section 504 of the Rehabilitation Act of 1973) (ክፍል 504 የ 1973 መልሶ የማጠናከር ሕገ ደንብ በመባል የሚታወቀው) **እክል ያለባቸውን (disabled) ተማሪዎች፣ በሚሰጡ አገልግሎቶች፣ ፕሮግራሞች እና ክንዋኔዎች፣ መድልዎ እንዳይደረግባቸው ይጠብቃል።** በተጨማሪም ዲሲፒኤስ፣ በዲስትሪክቱ የሚኖሩ እና ሁኔታዎች ወይም አገልግሎቶች እንዲመቻችላቸው (may need accommodations) የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችን፣ ለይቶ ማወቅ እና የእክላቸውን ደረጃ መመዘን ይኖርበታል። ልጅዎን ዐቢይ በሆነ በሕይወት እንቅስቃሴ ላይ በከፍተኛ ደረጃ ጫና ሊያሳድር እና ሊያውክ የሚችል **እክል** አለበት ወይም ሊኖርበት ይችላል ብለው **የሚያውቁ ወይም የሚጠረጥሩና** በዚህ የተነሣም በክፍል (Section) 504, ሥር ሁኔታዎች ተመቻችተው እንዲገኙለት (need accommodations) ይፈልጋል የሚሉ ከሆነ **የልጅዎን መምህር ወይንም የትምህርት ቤቱን የ 504 አስተባባሪ አነጋግሩ።** ምንኛውም ዐይነት ጥያቄ ካለዎት የዲስትሪክቱን የተማሪዎች Targeted Student Support ጽሕፈት ቤቱን በ 202-299-2005 ደውለው ያነጋግሩ።

## የክትባቶችዎን እና የጤና ምርምር ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቶችዎን ወቅቱን የጠበቁ እንዲሆኑ ያድርጉ

እንደ ወላጅነትዎ/አሳዳጊነትዎ፣ ልጆች በትምህርት ቤት በርካታ በሽታዎችን ሊያዛምቱ እንደሚችሉ ያውቃሉ። **ክትባቶች፣ ልጆችን እጅግ በጣም አደገኛ ከሆኑ በሽታዎች ይከላከላሉ።** ልጆች ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት እንዲከተቡ ሕጉ የሚጠይቀው ለዚህ ነው ፤ **የልጅዎ ክትባቶች ወቅቱን ጠብቀው የማይገኙ ከሆነ፣** እባክዎን አሁኑኑ በፍጥነት **ከልጅዎ ሀኪም ጋር ቀጠሮ ያድርጉ።** አንዳንድ ክትባቶች ተመልሶ መወሰድ የሚገባው ከአንድ ልክ መጠን በላይ ክትባት ይጠይቃሉ ።

ለየእድሜው ስለሚያስፈልገው የክትባት ማስታወሻ ለማየት **በመመዝገቢያዎ ማጠናቀሪያ አቃፊ ውስጥ በራሪ ወረቀቱን (flier) ይመልከቱ።** አሁን የዲሲ ሕግ፣ በየትኛውም የክፍል ደረጃ የሚገቡ ልጆች ሁሉ፣ አጠቃላይ ሁሉ አቀፍ የሆነ የጤንነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በየዓመቱ እንዲያቀርቡ ይጠይቃል። **እያንዳንዱ ተማሪ** በአለፉት 365 ቀናት ውስጥ የሰውነት ምርመራ ያጠናቀቀ መሆኑን የሚያመለክት **አጠቃላይ ሁሉ አቀፍ የሆነ የጤንነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማቅረብ ይኖርበታል። ከእድሜ ጋር የሚመጣጠኑ ክትባቶች የተወሰዱ ለመሆናቸው በአጠቃላዩ ሁለ አቀፍ የጤንነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ላይ መመዝገብ አለበት።**

## ዲሲፒኤስ በጥሩ ዋጋ ጥሩ የምገብ አማራጮችን ለማግኘት እየጣረ ነው

የ **DCPS Office of Food & Nutrition Services (የዲሲፒኤስ የምግብ እና የአልሚ ምግብ አገልግሎቶች)** በየትምህርት ቤት ምግብ ቤቶች፣ ለጤና ተስማሚ የሆኑ ገንዘብ እየተከተተ ምግብ የሚገዛባቸው ማሽኖች (vending machines) እና ሰላጣ መሰል ምግቦች የሚሸጡባቸው (salad bars) የመሳሰሉትን ጨምሮ፣ **ለሚቀጥለው ዓመት አዲሲ የምግብ አማራጮችን** ለማቅረብ ጥረት ያደርጋል። የሚቀርቡ የምግብ ዐይነት ዝርዝሮችን ለማየትና ጽሑፉን ለማተም፣ በትምህርት ቤትዎ ምግብ ቤት ምን አዲስ ሁኔታ እንዳለ ለማንበብ፣ ወይም በዚሁ ላይ አስተያየት ለመሰንዘር www.dcps.dc.gov/DCPS/foodservices ን ይቃኙ።

## በትምህርት ቤት ስለ ሚጠበቅ የጠባይ ሥርዓት ደንብ (Behavior Code) ከልጅዎ ጋር ይወያዩ

የ **ዲሲፒኤስ የተማሪ የጠባይ ሥርዓት ደንብ ምዕራፍ 25 DCMR (DCPS Students behavior, code Chapter 25 DCMR)** ሠላም ለሰፈነበት የትምህርት ክልል ድጋፍ ለማድረግ እና ለተማሪዎች፣ ቤተሰቦች እና ለትምህርት ቤት መምህራንና ሠራተኞች፣ ተገቢነት የሌለው በትምህርት ቤት የሚታይ ጠባይ ስለሚያስከትለው ውጤት ግልጽ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው። በ dcps.dc.gov, ድረገጽ ላይ ስለሚገኘው ምዕራፍ 25 ን ጨምር (“In the Classroom” እና “Expectations of Students” በሚለው ላይ በኮምፒዩተር መጠቆሚያ ጠቆም ያድርጉ።) **ተማሪዎች እና ወላጆች፣ የሚከተሉትን ነጥቦች መቃኘት (review) አለባቸው።**

- ተገቢነት ለሌለው ጠባይ የሚደረገውን ምላሽ በተመለከተ፣ ዲሲፒኤስ፣ በትምህርት ክፍሎች እና በትምህርት ቤት ደረጃ ተገቢነት የሌለው ጠባይ እንዳይፈጠር ይከላከላል፣ ጣልቃ ገብ ሥልቶችንም ያበረታታል።
- የተማሪ ጠባይ፣ የትምህርት ቤት ማኅበረሰቡን ሠላማዊ የትምህርት እንቅስቃሴን የሚያውክ ሆኖ ከተገኙ፣ ትምህርት ቤቶች ሁከት ፈጣሪውን ተማሪ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ፣ ከክፍል የማስወጣት (in-school suspension)፣ ከትምህርት ቤት ውጪ እንዲቆይ ማድረግ (out-of-school suspension)፣ እና ከትምህርት ቤት ጭራሽ ማባረር ወይም ማሰናበት (expulsion) የመሳሰሉትን ጨምሮ ሰፊና በርካታ የቅጣት እርምጃዎችን ተፈጻሚ ማድረግ ይችላሉ።
- ተማሪዎች በምዕራፍ 25 ላይ ተነድፎ በቀረበው መሠረት ሙሉ የሆኑ ሕጋዊ መብቶች እንዲኖራቸው ይደረጋል።

የዲሲፒኤስ ሕጋዊ የሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎችን በተመለከተ የበለጠ መረጃ ለማግኘት **202-299-2005 ይደውሉ።**

*መድልዎ አልባ ማስታወቂያ ። በስቴቱ እና በፌድራላዊ ሕጎች መሠረት፤ የዲስትሪክ ኦፍ ኮሎምቢያ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች፣* ይሆናል ተብሎ በሚገመት ወይም ነው ተብሎ በሚታመን፤ በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በመጡበት ብሄራዊ ሀገር፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በአእምሮ ሁኔታ፡ በአቋምና በመልክ፣ በግበረ ሥጋ ምርጫ ዝንባሌ፣ ትዳር በመያዝና ባለማያዝ፣ ለመሆን በሚመኙት ወይም በሚመርጡት የጾታ ዝንባሌ፣ በቤተሰብ ማኅበራዊ ደረጃ፣ የቤተሰብ ኃላፊ በመሆንና ባለመሆን፣ በትምህርት ደርጃ፣ በፖለቲካ ዝንባሌ፣ በዘር ተፈጥሮ በሚገኝ መረጃ *(genetic information)*፣ አንዳች ዐይነት እክል በመኖር ምክንያት፣ *(disability)*፣ በገቢ ምንጭና መጠን ምክንያት፡ የቤተሰብ አምባጓሮ ተጠቂ በመሆን፣ በመኖሪያም ክልል ሆነ ወይም በሚሠሩት ሥራ ዐይነት መድልዎ እያደርግም ። ለተጨማሪ ሙሉ መረጃ http://dcps.dc.gov/DCPS/About+DCPS/Human+Resources/Notice+of+Non-Discrimination.ን ይቃኙ